# የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነት መመሪያ ቁጥር 1027/2017

Agricultural Producer and Distributor Relations Directive No. 1027/2017

ግብርና ሚኒስቴር
Ministry of Agriculture

መስከረም 28፥ 2017

## መመሪያ ቁጥር 1027/2017

## የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነት መመሪያ

የፌደራል መንግስት የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን ባወጣው አዋጅ ቁጥር 1289/2015 አንቀጽ 26 ንኡስ አንቀጽ 2 ለግብርና ሚኒስቴር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "**ስለ ግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነት መመሪያ ቁጥር 1027/2017**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ **"አዋጅ"** ማለት የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነት ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 1289/2015 ነው፤

2/ **"ባለስልጣን"** ማለት የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ወይም በክልል የግብርና ግብዓትና ምርትን ጥራት ለመቆጣጠር የተቋቋመ አካል ነው፤

3/ **"የቴክኒክ ግብረ ኃይል"** ማለት አግባብ ባለው አካል የምርት መጠን ወይም ጥራት መቀነስ ወይም ሙሉ በሙሉ መጥፋት ወይም መጨመር መንስኤዎችን ለማጥናት፤ የግብርና ምርት ውል አሰራር ሙያዊ ድጋፍና ክትትል የሚያደርግ ከራሱና ከሶስተኛ ወገን የሚመለከታቸው ባለሙያዎች የሚደራጅ ነው፤

4/ በአዋጁ የተሰጠዉ ትርጓሜ በዚህ መመሪያም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## በግብርና ምርት ውል አስመራች ለአምራች ስለሚሰጥ የድጋፍ ወሰንና አፈጻጸም

3. **በግብርና ምርት ውል  ስለሚሰጥ የድጋፍ ወሰን**

   1/ ለዚህ አንቀጽ ዓላማ "በሙከራ ደረጃ" ማለት አንድ የተሻሻለ አሰራር ወይም የግብርና ቴክኖሎጂ በሰርቶ ማሳያ ደረጃ ውጤታማነቱ እስኪረጋገጥ የሚከናወን ተግባር ነው፤

2/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የግብርና ምርት ውሉ የተቀናጀ ውል ከሆነ አስመራቹ የግሉ የሆነ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን በሙከራ ደረጃ በተመረጡና ማዕከላዊ ቦታዎች ለሚገኙ ሞዴል አምራቾች በስፋት ማስተዋወቅ ይኖርበታል::

3/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የግብርና ምርት ውሉ የተማከለ ውል ዓይነት ከሆነ አስመራቹ በአምራቹ አጠገብ የምርት ማዘጋጃ እና ማከማቻን የመገንባት ወይም ከሶስተኛ ወገን በኪራይ የማመቻቸት እና የማያጓጓዝ ተግባርን ማከናወን አለበት፡፡

4/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የግብርና ምርት ውሉ የባለብዙ ተዋንያን ውል ዓይነት ከሆነ፡-

ሀ) ለተዋዋዮች በሶሥተኛ ወገን የሚሰጠውን ድጋፍ ዓይነት እና አግባብ ያለው አካል ሊኖረው ስለሚገባው ድርሻ በግልጽ የተቀመጠ የመግባቢያ ሰነድ መኖር አለበት፤

ለ) የመግባቢያ ሰነዱን አግባብ ያለው አካል ከተዋዋይ ወገኖች እና ድጋፍ ከሚሰጡ ከሶሥተኛ ወገኖችጋር በመሆን ያዘጋጃል::

ሐ) የሶሥተኛ ወገን ሚና የተዋዋዮችን ውል የሚጣረስ ሆኖ ከተገኘ የተዋዋዮች ውል ገዢ ይሆናል፤

5/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የግብርና ምርት ውሉ የአገናኝ ውል ዓይነት ከሆነ፡-

ሀ) አምራቹን መወከል የሚችሉት የአምራች ህጋዊ ወኪል፤ የህብረት ሥራ ማህበር፣ የዘርፍና የሙያ ማህበራት፣ የግል እና የመንግስት የትምህርት ተቋማት፣ የመንግስትና የግል የምርምር ተቋማት፣ የሲቪክ ማህበራትና ድርጅቶች ወይም ሌላ ሶስተኛ ወገን አገኛኝ ሊሆን ይችላል፤

ለ) አምራቹ እንዲወክለው የወሰነውን አገናኝ ህጋዊነት አስመልክቶ ለአስመራቹ በቂ ማስረጃ ወይም መረጃ መስጠት አለበት፤

ሐ) አምራቹን የሚወክለው አገናኝን ሚና ወሰን በተመለከተ ተዋዋዮቹ በውላቸው በግልጽ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል፤

መ) አገናኝ ስለሚኖረው ሚና መወሰን እንደተጠበቀ ሆኖ አምራች ከአስመራቹ ማግኘት በሚገባው ግብዓትና የቴክኒክ ድጋፍ ላይ አሉታዊ ሚና መጫወት የለበትም::

4. **ስለ ግብርና ምርት ዉል ድጋፍ**

1/ ለዚህ አንቀጽ ዓላማ **"የመልካም ግብርና አሰራር"** ማለት ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድጉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን እና የግብርና አሰራሮችን የአፈርን ለምነትን በማይጎዱ፣ አከባቢን በማይበክሉ፣ በኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እሴቶች ላይ አሉታዊ ጫና በማያስከትልበት ሁኔታ መጠቀም ነው፤

2/ ለዚህ አንቀጽ ዓላማ **"የግብርና ኤክስቴሽን አገልግሎት"** ማለት በግብርና ምርት ውል የተሰማሩ አምራቾችን በቴክኖሎጂ፣ በምርምር፣ በአሰራር፣ በቴክኒክ እና ሌሎች ድጋፎችን በማድረግ አምራቹ በፈለገው እና ደረጃውን የጠበቀ ምርት ለማምረት የሚደረግ የድጋፍ ዓይነት ነው፡

3/ **ግብርና ምርት ዉል ድጋፍ፡-**

ሀ/ ከመልካም ግብርና አሰራር አንፃር የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት፤

ለ/ አስመራቹ የራሱን ባለሙያዎች በመቅጠር ወይም ሶስተኛ ወገንን በመወከል ቀጥታ ከአምራቾች የግብርና ምርቱን በገባው ውል መሰረት መሰብሰብ፤

ሐ/ አስመራቹ በሚቀጥረው ባለሙያ ውል ለገባው አምራች በአመራረት እና ርክክብ ሂደት የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፤ የምርት ጥራት ቁጥጥር ሥራዎችንም ማከናወን፤

መ/ አስመራቹ ከአምራቹ ጋር በሚገባው ውል መሰረት የግብዓት፣ የክትትልና የድጋፍ ተግባርን በራሱ ወይም በሶስተኛ ወገን መስጠት፤

ሊሆን ይችላል።

5. **በሶስተኛ ወገን ስለሚሰጥ የድጋፍ ዓይነትና የአፈጻጸም መሰፈርት**

ለአምራቹ የሚሰጡ ማበረታቻዎች የግብርና ምርታማነትን እና ጥራትን የሚያሳድጉ ግብዓቶችን ከግምት ያስገባ መሆን አለበት።

## ክፍል ሦስት

## ውልን ስለሚለውጡ ሁኔታዎች

6. **ስለ ምርት ዋጋ መጨመርና መቀነስ**

በምርት ርክክብ ጊዜ በውሉ ከተገለጸው ዋጋ ሲጨምርና ሲቀንስ ስለሚደረጉ ማሻሻያዎች፡-

1/ እንደአስፈላጊነቱ ወቅታዊ የማምረቻ እና የገበያ ወጪ፣ የምርት ሽያጭ ዋጋን ከግምት ውስጥ በማስገባት የምርት ዋጋን ተዋዋይ ወገኖች ክለሳ ሊደርጉ ይችላሉ፤

2/ የዋጋ ማሻሻያ ለማድረግ የሚያስችላቸውን ዝርዝር ሁኔታ በውላቸው ላይ ካላስቀመጡ ግን በሚከተሉት ሂደቶች መሰረት የዋጋ ማሻሻያ ሊያደርጉ ይችላሉ፤

ሀ) በወቅታዊ ዋጋ ላይ ልዩነት ሲኖር ሁለቱ ወገኖች በጋራ በመነጋገር በስምምነት መፍታት ይችላሉ፣

ለ) ከላይ በፊደል ተራ "ሀ" የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ስምምነት ላይ ካልደረሱ ሁለቱ ወገኖች በሚመርጡት አንድ የጋራ አደራዳሪ አማካኝነት ስምምነት ሊያደርጉ ይችላሉ፣

ሐ) ከላይ በፊደል ተራ "ለ" በተገለጸው መሰረት በአደራዳሪው አማካኝነት መግባባት ላይ ካልደረሱ ተደራዳሪዎቹ የየራሳቸውን አንድ አንድ ሰው መርጠው የሚመለከተው አግባብ ያለው አካል ሊያደራድራቸው ይችላል፣

መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ "ሀ እስከ ሐ" በተደነገገው ስምምነት ላይ ካልደረሱ በአዋጁ መሰረት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ይዳኛሉ።

## 7. የምርት መጠን ሲቀንስ ወይም ሲጨመር

1/ የምርት መጠን ሲቀንስ አምራቹ ውል እንደጣሰ ተቆጥሮ ኃላፊነት የሚወስደው፡-

ሀ) በአስመራቹ የተሰጠውን የግብርና ግብዓት መጠቀም ትቶ ከውሉ ውጭ ሌላ የተጠቀመ እንደሆነ፣

ለ) በአስመራቹ በተሰጠው የቴክኒክ ድጋፍ መሰረት ሳይጠቀም ሲቀር፣

ሐ) ምርቱን ከሰበሰበ በኋላ ለራሱ ሲያስቀር ወይም ለሌላ ወገን ሲሸጥ፣

መ) በአስመራችና አምራች ውል የተጠቀሱና በአምራቹ ሊተገበሩ የሚገባቸው ሌሎች ጉዳዮች ሳይተገበሩ ሲቀሩ እና፣

ሠ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ "ሀ" እስከ "መ" የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የሚኖራቸው በሶስተኛ ወገን እና አግባብ ባለው አካል የጋራ የቴክኒክ ግብረ ኃይል ሪፖርት ሲረጋገጥ፤

ነዉ።

2/ የምርት መጠን ሲቀንስ አስመራቹ ውል እንደጣሰ ተቆጥሮ ኃላፊነት የሚወስደው፡-

ሀ) ለአምራቹ የሰጠው የግብርና ግብዓት በተቆጣጣሪ ባለስልጣን ያልተመዘገበ ወይም ውጭ ሀገር ተመዝግቦ በሀገር ውስጥ ዝርዝር ያልተካተተ ወይም ጥራቱ ያልተረጋገጠ ከሆነ፣

ለ) ለአምራቹ የሰጠው የዕጽዋት እና የእንስሳት ተባይ ወይም በሽታ መከላከያ መድሃኒት በተቆጣጣሪ ባለስልጣን ወይም ውጭ ሀገር ተመዝግቦ በሀገር ውስጥ ዝርዝር ያልተካተተ፣ ያልተመዘገበ ወይም ጥራቱ ያልተረጋገጠ ከሆነ፣

ሐ) ለአምራቹ ሊሰጠው የሚገባ የግብዓት ወይም የቴክኒክ ድጋፍ በግብርና ምርት ውሉ በተቀመጠው ጊዜ፣ ጥራት እና በሚፈለገው መጠን ልክ ሳይሰጥ ሲቀር፣

መ) አስመራቹ በየደረጃው ባሉ የስነልክ ተቆጣጣሪ አግባብነታቸው ያልተረጋገጠ ሚዛን ወይም ሌላ መለኪያ በመጠቀሙ፣

ሠ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ “ሀ” እስከ “መ” የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የሚኖራቸው በሶስተኛ ወገን እና አግባብ ባለው አካል የጋራ የቴክኒክ ግብረ ኃይል ሪፖርት ሲረጋገጥ፤

ነዉ፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከአቅም በላይ በሆነ አስገዳጅ ኃይል የተነሳ ምርትና ምርታማነት ቢቀንስ በአዋጁ አንቀጽ ”17” መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

4/ የምርት መጠን በሚከተሉት ምክንያቶች አምራቹ ጨምሮ ሲገኝ ውል እንደተጣሰ ይቆጠራል፤

ሀ) በውል ከተያዘው ማሳ ውጭ የተሰበሰበ ምርት ከተጨመረ፤

ለ) የግብርና ምርት ማምረት ውልን ዓላማን በሚጻረር መልኩ ምርት እንዲጨምር ከተደረገ፤

5/ አምራች አስመራች ባልገመተው ሁኔታ ሙሉ የአመራረት ምክረ ሃሳብ ጥንቅርና አሰራር ተጠቅሞ ውል ከተገባው ምርትና ምርታማነት ጨምሮ ቢገኝ አስመራች ስለሚረከብበት ሁኔታ በውሉ መካተት አለበት፡፡

## 8. የምርት ጥራት ሲጓደል የውል አፈጻጸም ሁኔታዎች

1/ ለምርት ጥራት መጓደል መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ክስተቶችና የውል ተፈጻሚነት ደረጃ በግልጽ በግብርና ምርት ውል ውስጥ መካተቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በሚከተሉት  ድንጋጌዎች በተመለከቱት ምክንያቶች የተነሳ በውሉ የተጠቀሰው ምርት ጥራት ሲቀንስ አምራቹ ወይም አስመራቹ ተጠያቂ ሊሆኑ ይችላሉ፤

1/ የምርት ጥራት ሲቀንስ አምራቹ ተጠያቂ የሚሆነው ፡-

ሀ) በሃገሪቱ የግብዓትና ምርት ጥራት ደረጃዎች መሰረት ጥራት የሚያጓድሉ ተብለው የተለዩትን ሁሉ በግብርና ምርቱ ውስጥ ከጨመረ፤

ለ) ውሃ በመጨመር የተፈቀደው የተፈጥሮ የእርጥበት መጠን ወይም ይዘትን ካዛባ፣

ሐ) በውላቸው ከተፈቀደው የግብርና ምርት መያዣ፣ መሰብሰቢያ፣ ማከማቻ፣ ማጓጓዣ ወይም ማቀዝቀዣ ውጭ ምርቱን በማስቀመጡ ወይም በማጓጓዙ ጥራት ሲያጓድል፣

መ) ተገቢውን የጸረ ተባይ ወይም የበሽታ መከላከያ መድሃኒት ባለመጠቀሙ የምርቱ ጥራት ቢጓደል፣

ሠ) ያልተፈቀደ ወይም በተዋዋይ ወገኖች በግብርና ምርት ውሉ ያልተጠቀሰ እና የግብርና ምርቱን ይዘት እና ጥራት የሚለውጥ ኬሚካል ከተጠቀመ፣

ረ) ሌሎች በግብርና ምርት ውል የተጠቀሱ ወይም በተክኒክ ድጋፍ ወቅት በጽሁፍ የተገለጹና በሁለቱም ወገኖች ተቀባይነት ያገኙ ጥራትን ሊጠብቁ የሚችሉ ምክረ-ሃሳቦች በአምራቹ በኩል ተግባራዊ ሳይሆኑ ሲቀሩ፤

ሰ) በውሉ ከተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ምርቱን ለአስመራቹ ባለማስረከቡ በሚደርስ የምርት ጥራት መጓደል፣

ሸ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከ “ሀ” እስከ “ሰ” የተጠቀሱት በሶስተኛ ወገን እና አግባብ ባለው አካል የጋራ የቴክኒክ ግብረ ኃይል ሪፖርት ሲረጋገጥ፤

ነዉ፡፡

2/ የምርት ጥራት ሲቀንስ አስመራቹ ተጠያቂ የሚሆነው፡-

ሀ) በግብርና ምርት ውሉ መሰረት ጥራትን መጠበቅ የሚያስችሉ ግብዓቶች ለአምራቹ ሳያቀርብ በመቅረቱ፣

ለ) በግብርና ምርት ውሉ መሰረት ጥራትን መጠበቅ የሚያስችል የቴክኒክ ድጋፍ ለአምራቹ ሳይሰጥ ቢቀር፣

ሐ) ያልተፈቀደ ወይም ግዜ ያለፈበት ወይም በግብርና ምርት ውሉ ያልተጠቀሰ እና የግብርና ምርቱን ጥራት የሚለውጥ ኬሚካል አምራቹ እንዲጠቀም ካደረገ፣

መ) በውሉ በተጠቀሰው የግዜ ገደብ ተገኝቶ ምርቱን ከአምራቹ ባለመረከቡ በሚደርስ የምርት ጥራት መጓደል፣

ሠ) ሌሎች ጥራትን ለመጠበቅ የሚያስችሉ እና በግብርና ምርት ውሉ የተጠቀሱትን ጉዳዮች ሳይፈጽም ቢቀር፣

ረ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ “ሀ” እስከ “ሠ” የተጠቀሱት በሶስተኛ ወገን እና አግባብ ባለው አካል የጋር የቴክኒክ ግብረ ኃይል ሪፖርት ሲረጋገጥ፤

ነዉ፡፡

## ክፍል አራት

## ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ሲፈጠር ስለማሳወቅ

**9. ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ሲፈጠር የማሳወቂያ ሂደት አፈጻጸም እና የግዜ ገደብ**

ከግብርና ምርት ተዋዋይ ወገኖች በኩል ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል በአዋጁ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሱት ክስተቶች በተፈጠረ ጊዜ፡-

1/ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ያጋጠመው አንደኛው ተዋዋይ ወገን ለሌላው ተዋዋይ ወገን እና ለሚመለከተው አግባብ ያለው አካል በ72 ሰዓት ውስጥ የተከሰተውን ሁኔታ ማሳወቅ ይኖርበታል፣

2/ ከአቅም በላይ የሆነው ሀይል በአንደኛው ወገን ላይ የደረሰ ሞት ከሆነ ለሌላው ተዋዋይ ወገን እና ለሚመለከተው አግባብ ያለው አካል ሞቱ ከተረጋገጠበት ቀን ጀምሮ በ72 ሰዓት ውስጥ የተከሰተውን ሁኔታ ወራሽ ወይም ተተኪው ማሳወቅ ይኖርበታል፣

3/ የተከሰተውን ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ በስልክ፣ በኢሜል፣ በጽሁፍ ወይም በአካል ማሳወቅ አለበት፤

4/ በአዋጁ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የጉዳት መጠን አምራቹ የገባዉን ግዴታ መፈጸም የማያስችለዉ መሆኑን አግባብ ያለዉ አካል በቴክንክ ግብረኃይል ሊያረጋግጥ ይገባዋል፤

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>የግብርና ምርት ውል ተሳተፊዎች መስፈርት እና  የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት አሰጣጥ</u>

**10. የተዋዋይ መስፈርት**

1/ ማንኛዉም ሰዉ አስመራች ለመሆን የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

ሀ) የግብርና ምርት ለማስመረት ፈቃደኝነት ወይም ፍላጎት ያለው፣

ለ) በዘርፉ ህጋዊ የንግድ ፍቃድ ማቅረብ የሚችል ወይም የተመዘገበ ሕብረት ሥራ ማሕበር፣

ሐ) የግብርና ምርት ውል ኢንቨስትመንት ፈቃድ ያለው፣

መ) በገለልተኛ ኦዲተር ኦዲት የተደረገ የአንድ ዓመት የሂሳብ ሪፖርት፣

ሠ) የንግድ ዕቅድ አዘጋጅቶ ማቅረብ የሚችል፣

ረ) ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች የመስጠት አቅምና ፍላጎት ያለው፣

ሰ) ግብአት የማቅረብ አቅምና ፍላጎት ያለው፣

ሽ) የመልካም አፈጻጸም ዋሰትና የሚሆን ከአምራች ጋር ለማስመረት እና ለመግዛት ከሚገባው ምርት ጠቅላላ የመግዣ ዋጋ 2 በመቶ በዝግ አካውንት ስለማስያዙ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፤

ቀ) አስመራች በግለሰብ ደረጃ ከሆነ የጋብቻ ሁኔታ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፤

2/ ማንኛዉም ሰዉ አምራች ለመሆን የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

ሀ) በግብርና ምርት ውል ትስስር ለመሳተፍ ፈቃደኛና ታማኝ የሆነ፣

ለ) ህጋዊ የሆነ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያለው ወይም ህጋዊ የሆነ ቢያንስ የአንድ ዓመት የመሬት ኪራይ ውል ያለው ለዓመታዊ ሰብሎች፤ ለቋሚ ሰብሎች እንደየሰብሉ አመራረት ባህሪ ተለዋዋጭ ቢሆንም ቢያንስ አስር አመት የመሬት ኪራይ ውል ሰነድ ማቅረብ የሚችል፤

ሐ) ለእንስሳት እና ዓሣ እርባታ፣ ማድለብ ወይም ለሌሎች ተመሳሳይ የልማት ተግባሮች ሲሆን እንደየተግባሩ ዓይነትና ባሕሪይ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል፤

መ) የግብርና ዕውቀትና ልምድ ያለው፣

ሠ) ለመማር ወይም ትክክለኛውን ምክረ-ሃሳብ ተከትለው ለመስራት ፈቃደኛ የሆነ፤

ረ) ለምርት ጥራትና መጠን የሚያስፈልጉ በአስመራች የሚቀርቡ ግብዓቶችና የቴክኖጂ ውጤቶችን በአግባቡ ለመጠቀም ፍቀደኛ የሆነ

ሰ) የጋብቻ ሁኔታ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፤

ሸ) ህብረት ሥራ ወይን ዩኒየን ከሆነ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ያለው፡፡

## 11.የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት አሰጣጥ

1. አንድ አስመራች በግብርና ውል ተመስርቶ የግብርና ምርትን ለማስመረት በሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ክልሎች እንዲሰማራ ሲጠይቅ የግብርና ሚኒስቴር የሚከተሉትን መስፈርቶች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡-

   ሀ) በግብርና ምርት ውል የብቃት ማረጋገጫ በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ መሰረት ለግብርና ሚኒስቴር ማመልከቻ ሲያቀርብ፣

   ለ) የግብርና ኢንቨስትመንት ፍቃድ፣

   ሐ) ህጋዊ ንግድ ፍቃድ፣

   መ) ስራውን በሚሰራበት ክልል ወይም በፌደራል ደረጃ ቢሮ ሲኖረው፤

   ሠ) የአንድ ዓመት በገለልተኛ ኦዲተር ኦዲት የተደረገ ሪፖርት ማቅረብ፤

   ረ) የንግድ ዕቅድ ማቅረብ የሚችል፤

   ሰ) ለህበረት ሥራ ማህበራት ሲሆን የምዝገባ የምስክር ወረቀት፤

ሸ) በሚሰማራባቸው ክልሎች አግባብ ባለው አካል እና ውልን ለመመዝገብ በተፈቀደልት አካል የተፈረመና ማህተም ያረፈበት የግብርና ምርት ውል ማጠቃለያ ቅጽ ለግብርና ሚኒስቴር ማቅረብ የሚችል፤

ቀ) የመልካም አፈጻጸም ዋስትና የሚሆን ከአምራች ጋር ለማስመረት እና ለመግዛት ከሚገባው ምርት መጠን ጠቅላላ የመግዣ ዋጋ 2 በመቶ በዝግ አካውንት ማስያዙንና፤

በ) የቴክኒክ ድጋፍ የሚያደረግ ባለሙያ

2. ማንኛውም ሰው በአንድ ክልል ብቻ በግብርና ምርት ውል መሰረት ለማምረት የብቃት ማረጋገጫ የምሰክር ወረቀት ሲፈልግ ከክልሉ አግባብ ያለው አካል የሚያገኝ ሆኖ፤

ሀ) በክልሉ አግባብ ያለው አካል የሚያወጣውን የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት ማሟላት ይኖርበታል፤

ለ) በክልሉ የሚያወጣው የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ካወጣው የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት በማይፃረር መልኩ ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

ሐ) የክልሉ አግባብ ያለው አካል የሚያወጣቸው የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 እና 11 ከተገለጹት ጋር እንዲስማሙ ማድርግ አለበት፡፡

**12. የሚኒስትር መስሪያ ቤቱ የግብርና ምርት ውል ማጠቃለያ ቅጽ አዘገጃጀትና ይዘት**

ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ክልሎች በግብርና ምርት ውል ተመስርቶ ለማስመረት ለሚሰማራ ሰው የሚዘጋጀው የሚኒስቴሩ መስሪያ ቤት የግብርና ምርት ውል ማጠቃለያ ቅጽ በአዋጁ አንቀጽ 5 እና 6 ላይ የተጠቀሰው የግብርና ምርት ውል አዘገጃጀት እና ይዘት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፤

1/ አስመራች የግብርና ምርት ውል የገባባቸው ወረዳዎችና ቀበሌዎች ዝርዝር ለክልል አግባብ ያለው አካል ማቅረቡን የሚያሳይ መረጃ፤

2/ የግብርና ማምረት ተግባሩ የሚከናወንበት ቦታ አድራሻ የሚያሳይና በጂፒኤስ የተደገፈ ካርታ ለክልል አግባብ ያለው አካል ማቅረቡን የሚያሳይ መረጃ፤.

3/ በውሉ የተካተቱ አምራቾች ብዛትና ውል የገቡበት የማሳ ስፋት፣ ግብርና ምርት ዓይነት፤ መጠንና የጥራት ደረጃ ማጠቃለያ የሚያሳይ መረጃ በክልል በኩል መቅረቡን፤

4/ የግብርና ምርት ውሉ ዓይነት እና ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በማጠቃለያ ቅጹ የሚያካትታቸው ሌሎች መረጃዎች፤

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>የውል ሀሳብ ማቅረቢያ፣ መመርመሪያ ጊዜ እና የውል ዘመን</u>

**13.የግብርና ምርት ውል ሃሳብን ለማቅረብና ለመመርመር የሚሰጥ የጊዜ ገደብ**

በአዋጁ አንቀጽ 4 የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆነው ተዋዋይ ወገኖች የውል መነሻ ሃሳብ ይዞ ለመቅረብ የሚከተሉትን ሁኔታዎች አስቀድመው ከግምት ማስገባት ይኖርባቸዋል፤

1/ ማንኛውም ተዋዋይ ወገን የግብርና ምርት ውል መነሻ ሀሳብ ይዞ የሚቀርበው ለእንስሳት ምርቶች ወይም ተዋጽኦ ከሆነ እንደ እንስሳቱ ዓይነትና የእንስሳቱ ተዋጽኦ እንዲሁም የአመራረት ባህሪ፣ ዝርያ እና የአመጋገቡን ስርዓት ግምት ውስጥ ያስገባ ሆኖ ቢያንስ አንድ ወር በፊት ማቅረብ አለበት፤

2/ ማንኛውም ተዋዋይ ወገን የውል መነሻ ሃሳብን ይዞ የሚቀርበው ውል ከሚገባበት የግብርና ምርት ማምረቻ ሥነ ምህዳር አኳያ የእጽዋቱ ዘር ወቅት ከመድረሱ ቢያንስ አንድ ወር በፊት መሆን አለበት፤

3/ የግብርና ምርት ውል መነሻ ሃሳብ የቀረበለት ተዋዋይ ወገን የውሉን ሁኔታዎች በአግባቡ ለመመርመር የሚወሰደው ጊዜ ከአስራ አምስት ተከታታይ ቀናት ያልበለጠ መሆን አለበትለ፡፡

**14.የግብርና ምርቶች የውል ዘመን**

ተዋዋይ ወገኖች በውል ሰነዱ የሚግቡባቸው የግብርና ምርት ውል ዘመን እንደ እንስሳቱ ወይም እጽዋቱ የአመራረት እና የሚደርሱበት የጊዜ ሁኔታ የሚለያይ ሲሆን ተዋዋይ ወገኖች በሚከተሉት አግባብ የውል ዘመንን ሊወስኑ ይችላሉ፤

1/ ለእንስሳት እና የእንስሳት ተዋጽኦ ወይም ምርቶች የውል ዘመን ተዋዋይ ወገኖች የምርቱን ባህሪ ግምት ውስጥ በማስገባት ሊወስኑ ይችላሉ፤

2/ ዓመታዊ ለሆነ ዕጽዋት የምርት ዘመኑ በሚወስደው ጊዜ ውስጥ የሚወሰን ይሆናል፣

3/ የሕይወት ዑደታቸውን ለመጨረስ ከአንድ ዓመት በላይ ወይም ሰንባች እጽዋት የሚፈልጉ የግብርና ምርቶች ወይም በባሕሪያቸው ልዩ የግብርና ምርት ውል ዘመን የሚያስፈልጋቸው ቋሚ የግብርና ምርቶች እንደ ምርቱ ዘመን የሚለያይ ሆኖ የውል ዘመኑ በአምራችና አስመራች ስምምነት የሚወሰን ይሆናል፣

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**15. አስተዳደራዊ እርምጃዎች**

1/ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች በጣሰ አምራች ወይም አስምራች ላይ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው አካል የሚከተሉት አስተዳደሪያዊ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡

ሀ) አስመራች በአምራቹ ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ኃላፊ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በግብርና ምርት ውል አምራችና አስመራች ቀጣይ ግንኙነት ላስከተለው አሉታዊ ተጽዕኖ እንደጥፋቱ ደረጃ ከግብርና ምርት ውል አሰራር ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል ተሳታፊ እንዳይሆን ይደረጋል፤

ለ) አምራቹ አነስተኛ ይዞታ ያለው አርሶ/አርብቶ አደር ከሆነ በአስመራቹ ላይ ላደረሰው ጉዳት በግብርና ውል መሰረት ተጠያቂ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ እንደጥፋቱ ክብደት ወደፊት በሚደረገው የግብርና ምርት ውል አሰራር ለተወሰነ ጊዜ እንዳይሳተፍ ይደረጋል፤

ሐ) አስመራቹ ወይም አምራቹ አግባብ ካለው አካል ሊያገኝ ይችል የነበረውን ድጋፍ ወይም ማበረታቻ እንዲያጣ ይደረጋል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል ተራ "ሀ" እስከ "ሐ" የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ያለው አካል የሚወስደው አስተዳዳራዊ እርምጃ፤

ሀ) የኢትዮጵያን ሕግ ሁሉ ያከበረ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፤

ለ) ከመውሰዱ በፊት የተፈጸመው ድርጊት የግብርና ምርት ውልን፣ አዋጁንና ይህን መመሪያ ያልተከተለ መሆኑና ሌላኛውን ወገን የጎዳ መሆኑን ቴክኒካል ግብረ ኃይሉ በማስረጃ አስቀድሞ ማረጋገጥ አለበት፤

ሐ) የሚወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ የተዋዋይ ወገንን የመደራደር አቅም አለመጣሱን ማረጋገጥ አለበት።

## 16.ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ይህ መመሪያ የተደነገገባቸውን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

## 17.መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በግብርና ሚኒስቴር ጸድቆ በፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገበና በተቋሙ ድህረ ገፅ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

**ግርማ አመንቴ (ዶ/ር)**

**የግብርና ሚኒስቴር**

**ሚኒስትር**